# በፈጠራ ወሬና ስም ማጥፋት ዘመቻ ኢትዮጵያ የጂኦ-ፖለቲካው ማራመጃ ልትሆን አትችልም

ሂዩማንራይስት ዎች የተባለው አለማቀፍ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ነኝ ባይ ድርጅት በኢትዮጵያ የሶማሌ ክልል ኦጋዴን አካባቢ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተፈጽሟል በሚል መሰረተ ቢስ ውንጀላ ላይ የተመሰረተ ሪፖርት ዛሬ ረፋዱ ላይ ይፋ አድርጓል፡፡ የድርጅቱ ሪፖርት ከመለቀቁ በፊት ደግሞ ይህንኑ መሰረተ ቢስ ውንጀላ በፕሬስ መግለጫ መልክ አሳጥሮ በትላንትናው ዕለት ለመገናኛ ብዙሃን ይፋ አድርጓል፡፡ ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል በሚል መርህ የሚመራው ይህ ድርጅት ያወጣውን መግለጫ መሰረተቢስ ነው ብሎ በማጣጣል ማለፍ ይችል የነበረ ቢሆንም ድርጅቱ ከሚያካሒደው የቅጥፋት ዘመቻ ጀርባ ያለውን ዋንኛ ምክንያት ማሳወቅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የኢፌዴሪ መንግሥት ይህን መግለጫ አውጥቷል፡፡

የሂዩማንራይትስ ዎች መግለጫ እንደከአሁን ቀደሙ ሁሉ በሶማሌ ክልል የሰብዓዊ መብት ጥሰትና የጦር ወንጀል ተፈጽሟል የሚል የፈጠራ ክስና ውንጀላዎችን የያዘ ነው፡፡ ድርጅቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን እውነታ ለመመልከት የሚስችል ነፃ ወኪል የሌለው መሆኑ የከአሁን ቀደም ሪፖርቶቹን ዋጋቢስ እንዳደረጋቸው ተገንዝቦ ከማሻሻል ይልቅ ያሁኑን ሪፖርት ኬንያ ላይ በመሆን ከክልላዊ መንግሥቱ ከድተዋል ያላቸውንና አንድ መቶ ያህል ሰዎችን ጨምሮ በማናገር እንዲሁም በሳተላይት ቀረፃ አገኘሁት በሚለው መረጃ ላይ ተመስርቶ እንዳጠናቀረው ያለአንዳች ሃፍረት ገልጿል፡፡ በዚህ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር መርጦ ባመጣለት ሰዎች ፖለቲካዊ ውንጀላ ላይ የተመሰረተ ሪፖርቱም የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት የጅምላ ግድያ ፈፅሟል፣ መንደሮችን አቃጥሏል፣ ህዝብን አሰቃይቷል፣ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ፈፅሟል እስከማለት ደርሷል፡፡ ይህን ሆን ተብሎ ታስቦበት የተቀነባበረ ስም የማጥፋት ዘመቻ ሪፖርትም የኢትዮጵያን መንግሥት አስተያየት ሳይጠይቅ ለመገናኛ ብዙሃን አዳርሶታል፡፡

የኢፌዴሪ መንግሥት ሂዩማናራይትስ ዎች የጀመረው አዲስ ዘመቻ እንዳልሆነና ጉዳዩ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ የፈጠራ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ በኢትዮጵያ ላይ የሚካሄደው ጆኦ-ፖለቲካዊ ፍላጎትን መነሻ ያደረገ ዘመቻ አካል እንደሆነ በጥብቅ ይገነዘባል፡፡ አገራችን በተሳካ የልማትና የዴሞክራሲ ጉዞ ውስጥ በምትገኝበትና በሁሉም መስኮች ውጤታማ መሆን ስትጀምር ሂደቱ ያላስደሰታቸው ወገኖች በየአቅጣጫው

ዘመቻ መክፈታቸው ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ በሶማሌ ክልል ያለውን ሁኔታ አስታኮ የሚካሄደው የቅጥፈት ዘመቻ ሲከሽፍ 6 ሚሊዬን ህጻናት በረሃብ አደጋ ተመተዋል የሚል መሰረተ ቢስ ዘመቻ የሚከፈትበት፣ ይህም በውሸት ላይ የተመሰረተ መሆኑ ሲጋለጥ እንደገና በኦጋዴን ላይ ሌላ ዙር የፈጠራ ውንጀላ በመክፈት የሚካሄደው የውሸት ዘመቻ ጉዳዩ ከኢትዮጵያ ጋር የሚያያዝ አንዳችም ችግር እንደሌለው አመልካች ነው፡፡ ለእኛም ሆነ ለማንም ታዛቢ ግልፅ እንደሚሆነው የዚህ ዘመቻ አቀነባባሪዎችና አራማጆች የሚነሱት ከራሳቸው የጂኦ-ፖለቲካዊ ፍላጎት ነው፡፡

በቅርቡ ይፋ እነዳደረግነው በኢትዮጵያ የሶማሌ ክልል የቻይና ነዳጅ ፈላጊዎችንና ሲቪል ኢትዮጵያውያንን አጋድሞ ያረደው የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር ከኋላ ያሰማሩትን ኃይሎች ፍላጎት ለማሟላት በማይችልበት ደረጃ ላይ እንዲገኝ ለማድረግ ችለናል፡፡ የመከላከያ ሰራዊታችን በዚህ አሸባሪ ኃይል ላይ በወሰደው የማጥቃት እርምጃ አሸባሪ ቡድን እንደተመታ ይታወቃል፡፡ ይህ አሸባሪ ቡድኑን ብቻ ሳይሆን በእርሱ ተማምነው በአካባቢው ጆኦ-ፖለቲካዊ ፍላጎታቸውን ለማሳካት ተስፋ አድርገው የነበሩ ኃይሎችን ሁሉ ክፉኛ አበሳጭቷል፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ ላይ መሰረተ ቢስ ውንጀላዎች በመደርደር የአገራችንን ስም ማጥፋት መርጠዋል፡፡

እነዚህ ኃይሎች አዲሲቱ ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት የተከበረባትና የመካለከያ ሰራዊቱም ከራሱ ህዝብ አልፎ በአፍሪካ ጭምር ከባድ ግዳጆችን በታላቅ ህዝባዊ መንፈስ እንደፈፀመ እያወቁ ይህንን በመሰለ አፍራሽ ዘመቻ ላይ የገቡበት ምክንያት ሌላ ሳይሆን በራሷ መንገድ ከድህነት መላቀቅ የጀመረች ጠንካራ ኢትዮጵያን ማየት ስለማይፈልጉ ነው፡፡ እነዚህ ኃይሎች በሁለት እግሯ የቆመች ኢትዮጵያ የጂኦ-ፖለቲካዊ ፍላጎታችን ማስፈፀሚያ ተቀጥላ አትሆንም የሚል ስጋት ውስጥ በመውደቃቸው በምንም አይነት ተጨባጭ መረጃ የማይደገፍ ውንጀላ እየደረደሩ ስም የማጥፋት ዘመቻውን አጧጡፈውታል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ መንግሥት መነሻና መድረሻው የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ማስከበር እንጂ ሌላ ባለመሆኑ ባሉባልታም ሆነ በሌላ ዘመቻ ኢትዮጵያን የጆኦ-ፖለቲካዊ ፍላጎት ማስፈፀሚያ ወይም ማሟያ መድረክ አድርገው መጠቀም የሚችሉ የሚመስላቸው ሁሉ ይህ ፈፅሞ የማይታሰብ እንደሆነ አጥብቆ ለማስገንዘብ ይወዳል፡፡ አሸባሪነትን መፋለም ብሔራዊ ጥቅማችንን ማስጠበቂያ መንገዳችን በመሆኑ እንደ ኦብነግ በመሳሰሉ አሸባሪ ኃይሎች ላይ የምንወስደውን እርምጃ ከኋላ ሆነው የሚልኳቸው ኃይሎች የሚሉትን ከምንም ሳንቆጥር እንደምንቀጥልበት ደግመን ደጋግመን እናሳውቃለን፡፡

ማስታወቂያ ሚኒስቴር

ሰኔ 05 ቀን 2000 ዓ.ም